
04·1r2·0070·1100

# ቹቹ በጉዳና

## መጽሐፍ ሁለት

From the Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሐንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES

ከዳንኤል ነጋሽ



ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ 1992

© ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ 1992

ስልክ ቁጥር 50 - 44 - 70
50 - 44 - 96

ፖ.ሣ.ቁ. 413 ኮድ 1110
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የሽፋን ሥዕል፡- ሥዩም ታደሠ
የውስጥ ሥዕል፡- መስፍን ሀብተማርያም

# ደፋሩ ቢራቢሮና የሰቀቀን ምሽት

ቶቶ ሲወድቅ የሆነ ነገር ቀዶ ነበር ቀልቀል የገባው። የዚህን ጊዜ፣«ዘራፍ! ዘራፍ! እኔ ደፋሩ ቢራቢሮ ትምህርት የማልማር፣ የማልሄድ ቢሮ» በማለት አንድ ሰው ፎክሮ ቶቶን አነቀው። «ጣራ ቀደህ ቤቱ የገባኸው ማነህ?»

«ቶቶ ነኝ። ልደናቅፎኝ ነው እባኬ» አለ እሻንጉሊቱ እየተንቀጠቀጠ።

አሞራው ከት ብሎ ሳቀና፣«እንደምን አደሩ አባባ ደፋሩ ቢራቢሮ፣ ይሄ ጓደኛዬ ነው። ቤቱ ጠፍቶበት ሲፈልግ፣ ሌሊት ውሾች ስላባረሩት እኔ አዳንኩት። ወደርሶ ይገፍው ስመጣ ደግሞ የላስቲክ ጎጆዎ ላይ ወጣበት» አላቸው።

«እንደምን አደርክ አሞራው፣ የኔ ጨልሌ ጮሌ! ይህ ቶቶ ነኝ የሚል ጓደኛህ ቤቱ ላይ የወጣው ለመሆኑ እይኑ ማጅራቱ ላይ ነው እንዴ ያለው?» አሉ እንደልማዳቸው እየቀለዱ።

«የለም አባ ቢራቢሮ፣ አይኑ ከግንባሩ ስርና ከጉንጩ በላይ እንደኮከብ እያበራ ነው።»

«ምን ሆነህ ነው የኔ ልጅ ቶቶ? አይዞህ አትደንግጥ» አሉና በጺማቸው ፊቱንና የአንገቱን ስር እያሻሹ ሲያሳስቁት ጊዜ ፍርሃቱ ለቀቀው። ከዚያም «ምነው የሽማግሌ ጉጆዬን አፈረስክብኝ? ምን ሆነህ ነው?» አሉት።

[illegible] Library of
ፍሥሐ አጥላው ወልደ ዮሃንስ
FESSEHA ATLAW WOLDE YOHANNES



«ቡዙና ሚጡ ናፍቀውኛል፡፡ ወትሮም ቤቴ ከደረስኩ የአሞራውና የሃምሣ እግርን ታሪክ እነግራቸዋለሁ እያልኩ ሳስብ ነው የተሳሳትኩት» አላቸው፡፡

«ሃሳብ አታብዛ፡፡ እግርህ የሚረግጠውን አይንህ ይየው፡፡ ያለበለዚያ እኔ ጉጆ ላይ ብቻ ሳይሆን ሰይጣን ላይም ልትወጣ ትችላለህ፡፡ ሰይጣን ደግሞ እንደኔ በጢሙ አያጫውትህም በቀንዱ ይጫወትብሃል እንጂ፡፡ ተጠንቀቅ፡፡»

«አባባ ቢራቢሮ፣ ሰይጣን ቢሉ አንድ ነገር ትዝ አለኝ፡፡ ይኸ አዲሱ ጓደኛዬ ሰዎች ሰይጣን ብለው ሲያባርሩኝ ነው ከጓደኞቼ የተለየሁት ብሎ አጫወተኝ፡፡ ደግሞም አሻንጉሊት ነኝ ይላል፡፡ እንደኛ እያወራ እንዴት አሻንጉሊት ሊሆን ይችላል? በሽተኛ ሳይሆን አይቀርም» አለ አሞራው፡፡

«በሽተኛ አይደለሁም! በፍፁም በሽተኛ አይደለሁም! ጉፈርም፣ አንተም አላመናችሁኝም እንጂ ዕውነቱን ነው:: እኔ ለቤዝዬ የተሠራሁ አሻንጉሊት ነኝ:: ለምን ዕውነቱን ስናገር አታምኑኝም?» አለ ቹቹ አምርሮ እያለቀሰ::

«የለም፣ የለም፤ አይዞህ አታልቅስ:: ይልቅ አንተ አሞራው፣ ጨልሌ ጮሌ፣ አንተም ቹቹ፣ ወዲህ ጠጋ በሉና አንድ ተረት ላውራላችሁ:: ተረቱን ስትሰሙ ቹቹ አሻንጉሊት መሆኑ አይገርማችሁም» አሉና ሁለቱን ህፃናት አቅፈው ተረቱን ሊያወሩላቸው ተዘጋጁ::

«ተረት፣ ተረት» አሉ ደፋሩ ቢራቢሮ::

«የላም በረት» ሲሉ መለሱ ቹቹና አሞራው::

«ጊላጉ የሚባል መስፈራርቾ ነበር» ሲሉ፣ አሞራው ጣልቃ ገባና፣

«ምንድነው መስፈራርቾ?» አለ::

«መስፈራርቾ ምን ማለት እንደሆነ በማወራልህ ተረት ውስጥ ስለምትሰማ ዝም ብለህ አዳምጥ» አሉትና ተረታቸውን ቀጠሉ::

«አንድ ገበሬ ነበር:: ሁሌ በእርሻ ሥራው ላይ ይለፋል፥ ይሰራል:: ክረምት ሲገባ በቆሎ ዘራ:: ነገር ግን የዘራውን በቆሎ ወፎች እየለቀሙ በሉበት:: በዚህ ሲበሳጭ ጓደኞቹ እንዲህ ሲሉ መከሩት 'ለምን መስፈራርቾ ሰርተህ እርሻህ ውስጥ አታቆምም?'

'ምንድነው መስፈራርቾ?' ሲል ገበሬው ጠየቀ:: 'መስፈራርቾ ማለትማ ከእንጨት፣ ከአሮጌ ኮትና ሱሪ የሚሰራ ሰው መሰል አሻንጉሊት ሆኖ የምትዘራውን በቆሎ ወፎቹ እንዳይለቅሙብህ የሚያደርግ ነው' ሲሉ መለሱለት:: ወዲያው ገበሬው ወደቤቱ ገባና አሮጌ ልብሶቹን አወጣ:: ከዚያም በተቆራረጡ እንጨቶች እግርና እጅ ያሉት አሻንጉሊት መሰል ነገር ሰራና ኮትና ሱሪውን አለበሰው:: ጭንቅላቱንም ከአሮጌ የእግር ኳስ ሰራለት:: አሮጌ ኮፍያ አደረገለት፤ ፊቱን ቀለም ቀብቶ አይንና ጆሮ ሰራለት:: ነገር ግን ስለረሳ አፍ ሳይሠራለት ቀረ:: ከዚያም ወደእርሻው ወስዶ ትንሽ ጉድጓድ በመቆፈር አቆመውና 'የዘራሁትን በቆሎ መጥተው የሚለቅሙ ወፎችን ጠብቅልኝ' አለው:: ጊላጉ በማለትም ስም አወጣለት::

«ከዚያን ዕለት ጀምሮም ጊላው የማስፈራራት ሥራውን ቀጠለ:: ወፎቹም ስለፈሩት ወደእርሻው ድርሽ አይሉም:: የተዘራው በቆሎም በየቀኑ እያደገ ሄደ:: ገበሬውም በጣም ደስ አለው:: **ጊላው** ግን ደስተኛ አልነበረም:: ሀምሌና ነሐሴ ከባድ የክረምት ጊዜ ስለሆነ **ዝናብ፣ ብርድና ቅዝቃዜ** ይፈራረቁበት ነበር:: ብርድና ብቸኝነቱም አሰቃየው:: **ከሌሎች ጋር** እንዳይነጋገር ወይም በፉጨት እንዳይጠራቸው ደግሞ **አፍ የለውም**:: በጣም አዘነ::

«በዚህ **ሁሉ ጊዜ** የተዘራው በቆሎ አድጎ ፍሬ አዘለ:: መስከረም ሲመጣ አደይ አበባ **ፈነዳ**፤ ምድርም በፀሐይ ድምቀትና በአበቦች ፍካት አማረች:: ያን ጊዜ አንድ **ነገር** ተፈጠረ:: አንዲት ትንሽዬ የመስቀል ወፍ እየበረረች መጣችና ጊላው ኮፍያ ላይ በማረፍ ታዋራው ጀመር::

'እንደምን አለህ መስፈራሪያ? ደህና ነህ? ስሜ የመስቀል ወፍ ይባላል:: በዓመት አንዴ በመስቀል ሰሞን ብቅ ስለምል ነው የመስቀል ወፍ የተባልኩት:: አንተ ክረምቱን ሙሉ ዝናብ ሲመታህና ብርዱ ጆሮ ጆሮህን ሲያሞልህ አይደል የከረምከው?' እያለች ብዙ **አወራችለት**፣ መዝሙርም ዘመረችለት:: በመጨረሻም 'አንተን ግን ምን ይዘጋሃል? ለምን አታናግረኝም?' እያለች ትኩር ብላ ብታየው አፍ የለውም::

'ውይ! ለካ አፍ የለህም፤ ሬው!' ብላ አፏጨችና 'አሁኑኑ ግሩም አፍ እሰራልህና ታዋሪኛለህ:: ጓደኞችም እንሆናለን' ብላ በመንቆሯ እየሰረሰረች አፍ አበጀችለት::



«ጊላጐ መስፈራርቸም ትንሺ የመስቀል ወፍ በፈፀመችለት ውለታ በጣም በመደሰት 'ትንሿ ጓደኛዬ የመስቀል ወፍ ሆይ፣ በጣም አመሰግንሻለሁ። ገበሬው ያመጣው ጥሬ ስላለ ጥቂት ውሰጂ' አላት። የመስቀል ወፍም ጥቂት ጥሬ ይዛ ሄደች። ከዚያ ወዲህ በጋውን ሁሉ ትንሿ ጓደኛው የመስቀል ወፍ በየቀኑ እየበረረች ትመጣና ለብዙ ሰዓት ያወራሉ።

«ቀስ በቀስ ፀሀያማው የበጋ ወቅት አልፎ የክረምቱ ወራት ተቃረበ። የመስቀል ወፍም ጊላጐን እንዲህ አለችው፤
'በጣም አዝናለሁ ጓደኛዬ ጊላጐ፣ እኔ የመስቀል ወፍ ክረምት አልወድም። ስለዚህ ወደሚመቸኝ መሄዴ ነው። ደህና ሁን' አለችው።
'በሚቀጥለው አመት ነይልኝ፤ እሺ?' አላት።
'እሺ እመጣለሁ፤ ቻው!' ብላ በረረች።

«ጊላጉ የመስቀል ወፍ ሰማይ ላይ ነጥብ አክላ ከዓይኑ እስክትሰወር አንጋጦ ተመለከተ:: የክረምቱ ጊዜ እንደተለመደው ቅዝቃዜና ብርድ ይዞ መጣ:: ጊላጉ በብርዱ ሳይቆራመድ በርታ አለና፣

'ውድ ጓደኛዬ የመስቀል ወፍ መስከረም ሲጠባ፣ አደይ አበባ ሲፈነዳና የመስቀል ደመራ ሲተከል በቶሎ ትመጣልኛለች' አለና ፈገግ በማለት ጓደኛው በሰራችለት አፉ እያፏጨ ስራውን ቀጠለ::»

ደፋሩ ቢራቢሮ ተረታቸውን ሲጨርሱም እንዲህ አሉ፣ «አንተ አሞራው ማወቅ ያለብህ ቺቺም ሆነ ሌላ እሻንጉሊት ሲያወራና ሊጫወት ስለሚችል ቺቺ የሚልህን ልታዳምጠው ይገባልና አታስቀይመው::»

ደፋሩ ቢራቢሮ በተናገሩት ሁሉ ቺቺ በጣም ተደሰተ:: አሞራው ግን፣ «ከተረቱ ይልቅ እኔን ያሳዘነኝ ጊላጉ እንደኛ በዝናብና በፀሐይ ብቻውን ውጭ መኖሩ ነው አለ::»

ደፋሩ ቢራቢሮ ቺቺን በተረቱ ካዝናኑት በኋላ ታሪኩን እንዲያጫውታቸው ጠየቁት:: ቺቺም ሳይጨምር፣ ሳይቀንስ ሁሉንም ነገራቸው::

«ከታሪክህ እንደተረዳሁት ቤዙና ሚጡን አግኝተህ ከነሱ ጋር መኖር ትፈልጋለህ:: ጉፈርንም ማግኘት ትፈልጋለህ፣ ክፉንችላ ደግሞ ጠላትህ ነው:: ስለዚህ እኔ ደፋሩ ቢራቢሮ ባለኝ ብልሃትና ጥበብ ተጠቅሜ ወዳጆችህን አፈላልግሃለሁ:: ጠላትህን ክፉንችላንም ቢቻል መክረን ወዳጅ እናደርገዋለን፣ እምቢ ካለም ከዚህ ሀገር ድራሹን አጠፋዋለሁኝ፤ አይዞህ!» አሉ ደፋሩ ቢራቢሮ::

ቺቺ ደስ እያለው፣ «ለምን ደፋሩ ቢራቢሮ ተባሉ?» አላቸው::

«አንድ ቦታ ስለማልቀመጥ ነው:: ቢራቢሮ አንድ ቦታ ትቀመጣለች? አትቀመጥም:: ወዲያ፣ ወዲህ ስትበር፣ ከአንዱ አበባ ወደሌላው ስትሻገር ትውላለች:: ደፋር ናት:: የምትፈራው ምንም ነገር የለም:: የኔ አበባዎች እናንተ ናችሁ:: ከአሞራው ወደቺቺ፣ ከቺቺ ወደሃምሣ እግር እያልኩ እኖራለሁ:: ቺቺን አሁን የምጠይቅህ ከነቤዙ ጋር በነበርክ ጊዜ የምታውቀውን ነገር ሁሉ

እንድትነግረኝ ነው። በተለይ ውሻ፣ ድመት፣ ርግብ ወይም ወፍ ይኖራቸው እንደሆነ ከነቀለማቸው ንገረኝ» አሉት።

«ኢካ የምትባል ዥንጉርጉር ድመት ብቻ ነች ያለቻቸው።»

«ኢካ የምትባለው ድመት ከቤት ትወጣለች?»

«አዎን፣ በየወሩ መጨረሻ ለሸርሽር አብራቸው ወደመናፈሻ ትሄዳለች።»

«ወደየትኛው መናፈሻ?»

«አላውቀውም። ግን አንድ ነገር ትዝ አለኝ።»

«ምንድነው? ንገረኝ።»

«የጉረቤታችን የሆነች አንድ ነጭ ደረቷ ላይ ብቻ ጥቁር ያለባት ኩኩ መለኮቴ የምንላት ርግብ አውቃለሁ።»

«ይሄ ጥሩ አጋጣሚ ነው» አሉ ደፋሩ ቢራቢሮ።

«ለምን? ቹቹ የሚፈልገው እኮ ቤዙንና ሚጡን እንጂ ድመት ወይም ርግብ አይደለም!» አለ አሞራው።

«ልክ ነህ አሞራው። ልክ ነህ የኔ ጩልሌ። እየህ፣ የቹቹ ጓደኞች ቤዙም ሆነች ሚጡ ከወላጆቻቸው ተለይተው ወደውጭ ስለማይወጡ ቶሎ ልናገኛቸው አንችልም። ድመትና ርግብ ግን ወደፈለጉበት ስለሚሄዱ ልናገኛቸው እንችላለን» አሉ።

«እሺ ድመቷ ኢካን ወይም ርግቧ ኩኩ መለኮቴን ብናገኝ ምን ይጠቅመናል?» ሲል አሞራው መልሶ ጠየቃቸው።

«ለምሳሌ፣ ኢካን ብናገኛት 'ውርር' ብለን በመጥራት አንገቷን በሲባጎ ማሰር ብቻ ነው። ከዚያ እሷ እየመራች እነቹቹ ቤት ትወስደናለች።ኩኩ መለኮቴን ብናገኛት ደግሞ እንደምንም ብለን እንይዛትና ደብዳቤ ሰጥተን እንልካታለን» አሉ ደፋሩ ቢራቢሮ።

«ድመቷን በወተት አባብለን እንይዛታለን፤ በሰማይ የምትበር ርግብ ግን እንዴት ትያዛለች?» አለ አሞራው።

ቹቹ ቀበል አደረገና፣ «እንዴ ኩኩ መለኮቴ እኮ የምትወደው ፋጩት አለ። ያን ስናፏጭላት በርራ ትመጣና አጠገባችን ታርፋለች።

ያኔ በቆሎ እየበተንን መያዝ ነው:: ሁሌ እንዲህ እናደርግ ነበር» አለ::

«አምራው መልስ አገኘህ? በጣም ጥሩ:: ያልገባህን ነገር መጠየቅህ ጥሩ ነው:: ቼቼም የምታውቀውን ለሌላ ማካፈልህ ተገቢ ነው:: አሁን መጀመሪያ ማድረግ ያለብን ምንድነው?» በማለት ደፋሩ ቢራቢሮ ሲጠይቁ፣ «የቼቼን ዘመዶች ፈልገን ማግኘት!» አለ አምራው::

«አዎ፣ ቼቼ በነገረን መሰረት በየወሩ መጨረሻ ወደ ሰናፊሽ ቦታዎች እንሄዳለን:: ሆኖም በዚህ ዓይነት በወር አንድ መናፈሻ ብቻ ነው ለማየት የምንችለው:: ከዚህ በተጨማሪ ሰው ወደሚሰበሰብበት ቦታ መሄድ ይኖርብናል:: ለምሳሌ ቤተ ክርስቲያን ብንሄድ ምናልባት ቼቼ የቤዙን እናት ወይም አባት ሊያገኛቸው ይችላል:: ለመሆኑ ቤቲ ትምህርት ቤት ስትሄድ የምትለብሰው ልብስ ሁሌ አንድ አይነት ነው?» ሲሉ አባባ ደፋሩ ቼቼን ጠየቁት::

«አይደለም፤ እናቷ የምታለብሳት የተለያዩ ልብሶችን ነው::»

«ልብሷን ማወቅ ደግሞ ምን ያደርግልናል?» አለ አምራው መሀል ገብቶ::

«እርሷን የማግኛ አንድ ቀላል ዘዴ ታይቶኝ ነው:: ወደትምህርት ቤት ስትሄድ ሁልጊዜ አንድ አይነት ልብስ ብቻ የምትለብስ ቢሆን ትምህርት ቤቷን እናውቀው ነበር::»

«የምትማርበት ትምህርት ቤት እንዴት በልብስ ይታወቃል?»

«ይታወቃል:: ብዙ ትምህርት ቤቶች የደንብ ልብስ ወይም ዩኒፎርም አላቸው:: ለምሳሌ ዩኒፎርሙ ከላይ ነጭ፣ ከስር ጥቁር ቢሆን እንዲህ ያለ የለበሰ ተማሪ መንገድ ላይ ፈልጎ በመከተል ትምህርት ቤቱ መሄድ ነው:: እዚያም ቤዙ የምትባል ልጅ እንፈልጋለን ብሎ በማስጠራት ከቼቼ ጋር ለማገናኘት ይቻላል» በማለት አስረዷቸው:: ትንሽ ቆይ እንዳሉም፣ «አረግ፣ አረግ ልጆቼን በረሀብ ጨረስኳችሁ አይደለም? በሉ ጥቂት ሳንቲሞች ስላሉኝ እንሂድና ቁርሳችንን ገዝተን ተካፍለን እንብላ» በማለት ይዘዋቸው ሄዱ::

አንድ ግንብ ስር በላስቲክና በሳጠራ የተሠራች፣ ውልግድግድ ባለ የእጅ ጽሑፍ «የጉዳና ልጆች ቁርስ ቤት» የሚል ፅሁፍ የተለጠፈባት ቤት ገቡ:: ጢብኛ፣ አምባሻና ዳቦ በሻይ እዘውም ቁርሳቸውን በሉ::



ከዚያ ኪወጡ አሞራውና ቹቹ የሚሸጥ ሙዝ በማየታቸው ተቁለጨለጩ:: ደፋሩ ቢራቢሮ እንዲገዙላቸው በጣም ፈለጉ:: ነገር ግን መጠየቅ ስለፈሩ ሙዝ፣ ሙዙን እያዩ አለፉ::

ደፋሩ ቢራቢር የአሞራውና የቹቹ አይን ሙዙ ላይ ሲንከራተት ተመልክተው አዘኑ:: የጉዳና ተዳዳሪ ህፃናት የሚፈልጉትን ሁሉ አያገኙም:: ምክንያቱም ወላጅም ሆነ ዘመድ አጠገባቸው ስለሌለ ማንም አያስብላቸውምና ነው:: ደፋሩ ቢራቢሮ ሙዙን ወደሚሸጡት አሮጊት ሲሄዱ ቹቹና አሞራውም ደስ እያላቸው ተከተሉዋቸው::

ሙዙ ስለተበላሸ ሞቅሙቋል:: በዚህም የተነሳ ዝንብ ወሮታል:: የሚሸጡት ሴትዮ በያዙት ቅጠል ዝንቦችን ያባርራሉ:: ዝንቦቹ በአቅራቢያው ባለ ቆሻሻ ላይ ሄደው ያርፋሉ፣ ተመልሰው ደግሞ ሙዙ ላይ ይሰፍራሉ:: አሮጊቷም ሲደክማቸው ይተውዋቸዋል::

ደፋሩ ቢራቢሮ ሁኔታውን ተመለከቱና፣ «ይቅር፣ ይቅር! ኑ ልጆቼ እንሂድ» አሉ። ህፃናቱ ሙዚ ስላልተገዛላቸው በጣም ቅር ተሰኙ። ይህንንም ቅሬታቸውን ደፋሩ ቢራቢሮ ወዲያው አወቁባቸው።

«ሙዙን ያልገዛሁላችሁ ስስቼ ሳይሆን ለእናንተው አስቤ ነው። የተበላሸ ሙዝ አብልቼ ላሳምማችሁ አልፈልግም።»

«ሴትየዋ ሙዙ የተበላሸ መሆኑን እያወቁ ለምን ይሸጡታል?» አለ አሞራው እንደተከፋ።

«በሴትየዋ መፍረድ አይቻልም፥ ለሳቸው የሸጠላቸው ሰው ነው መጥፎ» አሉ ደፋሩ ቢራቢሮ።

«ማነው ለሳቸው የሚሸጥላቸው?»

«አንዳንድ የፍራፍሬ መሸጫ ቤቶች ናቸው ይህን የሚሠሩ። ሲበላሽባቸው ሰብስበው መጣል ወይም ዝንብ እንዳይራባበት ቆፍረው መቅበር ሲገባቸው ለድሆች ይሸጡታል። ለእናንተም አሁን የአምስት ሳንቲም የተበላሸ ሙዝ ባበላችሁ በኋላ በብዙ ብር ብትታከሙት የማይድን በሽታ ነው የሚይዛችሁ። የጉዳና ተዳዳሪ ህፃናት በመሆናችሁ። የሚረዳችሁ ሰው ህመሙ ሲገድላችሁ ይችላል» በማለት አስረዷቸው።

ጥቂት እንደተጓዙ ከአንድ የአውቶቡስ ተሳፋሪዎች ማረፊያ (ፌርማታ) ደረሱ። መጠለያዋ ፍርስርስ ያለች ናት።

«እዚች ጥላ ሥር አረፍ እንበልና አንድ ተረት ልንገራችሁ» አሉ ደፋሩ ቢራቢሮ ቁጭ እያሉ። ልጆቹም ቁጭ ብለው በጉጉት ይመለከቷቸው ጀመር።

«አንድ ፋብሪካ ውስጥ በትንሽ ደሞዝ ተቀጥሮ የሚሰራ ድሀ ሰው ነበር» አሉና ጀመሩ ደፋሩ ቢራቢሮ። «ይኸ ሰው ከሁለት ልጆቹና ከሚስቱ ጋር በሰላምና በደስታ ይኖር ነበር። ሁልጊዜም ልጆቹን ጨዋታና መዝሙር ያለማምዳቸዋል። ማታ፣ ማታ ደግሞ አስደሳች ታሪኮችንና ተረቶችን ያወራላቸዋል። የተረት መፅሀፍም ያነብላቸዋል።

«በዚህ ድሀ ሰውዬ ቤት አቅራቢያ አንድ ሀብታም ሰው ይኖር ነበር። ሀብታሙ ሰውዬም በድሀው በጣም ይናደድበት ጀመር።

ምክንያቱም ድሀው ሰውዬ በቂ ገንዘብ ሳይኖረው ከቤተሰቡ ጋር ተደስቶ ስለሚኖር ብቻ ነው።

በመጨረሻ ሀብታሙ ሰውዬ ድሀውን ወደቀጠረው ባለፋብሪካ ሄደና 'ፋብሪካህ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሠራ አንድ ጥጋበኛ ሰውዬ አለ። የሚኖረው ከኔ ቤት አቅራቢያ ነው። ሠፈሩን ሁሉ በጩኸት ይረብሻል። በሱ ረብሻ የተነሳ እንቅልፍ እንኳን መተኛት አልቻልኩም። ስለዚህ አንተ ዘንድ እንዲሠራ አልፈልግምና አባርልኝ' አለው። የፋብሪካው ባለቤትም ድሀውን ከስራ አባረረው።

«ድሀውም ከስራ ከተባረረ በኋላ ሌላ ስራ ማግኘት በፍፁም አቃተው። የነበራቸውን ምግብ በሙሉ እሱ፣ ሚስቱና ልጆቹ ስለበሉት አለቀ። በመጨረሻም ከዕቃዎቹ ውስጥ የቀረችውን አንድ ጎድጓዳ ሣህን ይዞ ምግብ ለመግዛት ወደሆቴል ቤት ሄደ።

«ምግቡን ገዝቶ ሲመለስም መንገዱ ጭቃ ስለነበር አዳልጦት ወደቀ። ምግቡም ተደፋበት። ከዚያም ሳህኗን አፀዳዳና ከፀሀይ እንድትከላከልለት ጭንቅላቱ ላይ ደፍቷት ወደሩቅ ሀገር ጉዞ ጀመረ።

«ብዙ ከተጓዘ በኋላ ባህር አገኘ። አባህሩ ዳርቻ አንዲት ጀልባ ነበረች። የጀልባይቱ ነጂ ሠራተኛ ይፈልግ ስለነበር ረዳት አድርጎ ቀጠረውና አብረው ጉዞ ጀመሩ። ጀልባይቱ ብዙም ሳትጓዝ ግን ማዕበል ተነሳና ሰጠመች። ጥቂት የጀልባይቱ ሠራተኞች ስብርባሪዋ ላይ እየተንጠላጠሉ ተረፉና እየተንሳፈፉ ወደ አንዲት ደሴት ደረሱ። ከጥቂት ሰዎች መካከል ድሀው ሰውዬ አንዱ ነበር።

«ደሴቲቱ ላይ ብዙ ሰዎች ንጉሣቸውን ከበው የተረፉትን ሰዎች ይመለከቱዋቸው ነበር። የደሴቲቱ ንጉስም እንግዶቹን በመልካም ስርዓት ተቀበላቸው።



«ድሀው ሰውዬ ያችን ሳህን ጭንቅላቱ ላይ አድርጓት ስለነበር፣ ንጉሡ 'ለምንድነው ያን ነገር ጭንቅላትህ ላይ ያደረግከው?' ሲል ጠየቀው።

'ጭንቅላቴን ከፀሀይ እንዲከለክልልኝ ነው' አለ ሰውዬው። ንጉሡ ሣህኗን ተቀብሎ ጭንቅላቱ ላይ ሲደፋት የፀሀይ ቃጠሎው ስለቀነሰለት በጣም ተደሰተና 'ይህን ነገር እፈልገዋለሁ። በሱ ፋንታ ምን እንድሰጥህ ትፈልጋለህ?' በማለት ጠየቀው።

'ወደ ቤቴ በሰላም መመለስ ብቻ ነው የምፈልገው' አለ ሰውዬው።

'በሰላም እንድትመለስ አደርጋለሁኝ። በቅድሚያ ግን ይህን ስጦታ ለአንተ ማበርከት እፈልጋለሁ' ብሎ አንድ ሳጥን ከፈተ። ሣጥኑ ውስጥ ከወርቅና ከአልማዝ የተሠሩ ውብ ጌጣጌጦች ሞልተውበታል። ቀለማቸውም ቀይ፣ ነጭ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫና ሰማያዊ ነበር።

«ድሀው ሰውዬ ጌጣጌጦቹን ከንጉሡ ተቀብሎ ሸጣቸው። ከዚያም ወደአገሩ ተመልሶ ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር መዘመር፣ መጫወት፣ መሳቅና ማንበብ ጀመረ።

ሀብታሙ ሰውዬ የድሀውን መዝሙርና ሳቅ እንደገና ሰማ፡፡ ድሀው ሰው ስላገኘው ገንዘብና ስለደሴቷ ንጉሥም ሰማ፡፡ ከድሀው የሚበልጡ ጌጣጌጦችን ለማግኘት እጅግ ስለጓጓም ስጦታዎችንና የወርቅ ጌጣጌጦችን ሰብስቦ ወደደሴቲቷ ንጉሥ ተጓዘ፡፡ ከብዙ ቀናት ጉዞ በኋላም የደሴቷን ንጉስ አገኘና ስጦታውን አቀረበለት፡፡

«የደሴቷ ንጉስም በጣም ተደሰተ፡፡ ሀብታሙን ሰውዬም አመስግኖ፣ 'ያለኝን በጣም ግሩምና ድንቅ ስጦታ ልሰጥህ ይገባል' አለው፡፡ ሀብታሙ ሰውዬም የሚሰጠውን የወርቅ ብዛት እያሰበ በጣም ጓጓ፡፡

በመጨረሻ ንጉሱ 'አንድ ጥሩ ሰው የሰጠኝ ድንቅ ስጦታ አለ፡፡ በዚህ ሀገር እንዲህ አይነት ውድ ዕቃ የለም' አለናም ከቅርጫት ውስጥ ድሀው ሰውዬ ሰጥቶት የነበረውን ሣህን አወጣና ለሀብታሙ አበረከተ» በማለት ደፋሩ ቢራቢሮ ተረታቸውን ጨረሱ፡፡ ከዚያም «ልጆቹ ቹቹና አሞራው፣ አያችሁ አይደል የዚህን የሀብታም ሥራ? ያ ሁሉ ሀብትና ንብረት እያለው በቃኝ ማለት አቅቶት ነው እንዲህ የሆነው» አሉ፡፡ ከዚያም «አረገኝ፣ እዚህ ተረት ስናወራ መሸ አይደል? በሉ ወደላስቲክ ጐጆዬ እንሂድ» በማለት ጉዞ ጀመሩ፡፡

ቹቹ፣ ቀጥሎ አሞራው፣ ከኋላ ደግሞ ደፋሩ ቢራቢሮ ተከታትለው ሲጓዙ፣ ቹቹ ሮጦ የሆነ ነገር ከመሬት አነሳ፡፡ አሞራው፣ «ብጋሬ! ብጋሬ!» እያለ ቢጮህም ቹቹ ያገኘውን ነገር ደብቆ አላሳይም አለ፡፡

በስንት ልመናና መለማመጥ ቹቹ ከመሬት አንስቶ የደበቀውን ዕቃ ደፋሩ ቢራቢሮ ተቀብለው ቢያዩት የህፃን ልጅ የአንድ እግር ጫማ ሆነ፡፡

«የሚጥዬ ጫማ ነው» እያለ ቹቹ ያለቅስ ጀመር፡፡

«ቆይ፣ ቆይ ቹቹ፣ የሚጡ መሆኑን በምን ታውቃለህ? የዚህን አይነት ጫማኮ ብዙ ህፃናት ሊኖራቸው ይችላል» አሉ ደፋሩ ቢራቢሮ እያባበሉት፡፡

«አውቀዋለሁ፣ የሚጡ ነው፡፡ ይኸው፣ እንዲሁ ቁልፍ ተነቅሏል፡፡ የራሷ የሚጡ ነው፡፡ ወይኔ ሚጥዬ . . . » እያለ ቹቹ ማልቀሱን ቀጠለ፡፡ አሞራውም ቢያባብለው ዝም አልል አለ፡፡

«ይሄኔ እኮ በዚህ ይሆናል ያለፉት? መቼ ይሆን ያለፉት? ጠዋት ይሆን ከሰዓት፣ ወይስ ማታ? በእግራቸው ሲሄዱ ይሆናል የጣለችው? ወይም ታክሲ

ሲሳፈሩ ይሆናል የወለቀባት? ኧረ ቤዝዬ፣ ኧረ ሚጥዬ ጋር ውሰዱኝ!» እያለ የሚጡ ነው ያለውን የአንድ እግር ጫማ አቅፎ ያለቅስ ጀመር:: ይኸኔ አሞራውም አብሮት አለቀሰ:: ደፋሩ ቢራቢሮም በጣም ስለአዘኑ የሚያደርጉት ጠፋቸው::



በመጨረሻ ግን ደፋሩ ቢራቢሮ ልጆች እንኮኮ ሲደረጉ ደስ እንደሚላቸው ስለሚያውቁ ቹቹን ተሸከመው እያባበሉ አሞራውን በማስከተል ወደላስቲክ ጐጆዋቸው ሄዱ::

ሰማዩ ቀልቷል:: እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ የቤዛዊት አባት «ፀሀይ እኮ እንዲህ ቀይ የምትሆነው ክኛ ተለይታ ልታድር ስለሆነ በጣም አልቅሳ አይኗ ስለሚቀላ ነው» ይል የነበረውን እያስታወሰ ሲተክዝ፣ አሞራው ቀስ ብሎ ደፋሩ ቢራቢሮን «ቹቹ በጣም ስለአዘነ እያጫወቱ አረሳሱት እንጂ» አላቸው::

«የኔ ልጅ ቹቹ፣ አንድ ተረት ላውራልህ፤ እስቲ እሺ በለኝ» በማለት አቀፉት:: ቹቹ ምንም አሻንጉሊት ቢሆን ህፃን ነው:: ህፃናት ደግሞ ተረት ላውራላችሁ ሲባሉ ደስ ስለሚላቸው ቹቹ ተረቱን ለመስማት በጉጉት ጠበቀ::

«አንዲት ሲንድሬላ የምትባል ቆንጆ ልጅ ነበረች» አሉና ጀመሩ ደፋሩ ቢራቢሮ። «ሲንድሬላ እናት የላትም። ምክንያቱም እናቷ በልጅነቷ ሞታባታለች። የሲንድሬላ እናት በተቀበረችበት ቦታ ላይ አንድ ዛፍ በቀለ። በዛፉም ላይ ነጫጭ ወፎች ይኖሩበት ጀመር።

«የሲንድሬላ አባት ለብቻው መኖር ስላልፈለገ ሚስት አገባ። አዲሷ ሚስቱ፣ ማለት የሲንድሬላ እንጀራ እናት በጣም ክፉ ሴት ነበረች። ሁለት ልጆች ሲኖሩዋት ሁለቱም እንደእናታቸው ክፉዎች ነበሩ። ምንም ሥራ አይሰሩም። ትምህርት ቤት ይሄዳሉ፤ ከዚያ መልስ የፈለጋቸውን ያህል ከጓደኞቻቸው ጋር ይጫወታሉ፤ ጥሩ ጥሩ ምግብ ይበላሉ። ቆንጆ፣ ቆንጆ ልብስም ይለብሳሉ። ለሲንድሬላ ግን ምንም ልብስ አይገዙላትም። ጥሩ ምግብም አያበሏትም። ትምህርት አትማርም። ጨዋታም አትጫወትም። በዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ የቤቱን ሥራ በሙሉ ያሠሯታል። ምንም ጓደኛ የላትም።

«የሲንድሬላ ጓደኞች በቤቱ ውስጥ ያሉት አይጦችና እናቷ መቃብር ላይ በበቀለው ዛፍ ላይ የሚኖሩት ወፎች ናቸው። የሲንድሬላ እናትና ልጆቿ በሌሉ ጊዜ እነዚህ ጓደኞቿ የቤቱን ሥራ ያግዟታል፤ ያጫውቷታልም። እንጀራ እናቷና ልጆቿ ሊመጡ ሲሉ ግን ወፎቹ በርረው ይሄዳሉ፤ አይጦቹም ወደጉሬያቸው ገብተው ይደበቃሉ።

«ሲንድሬላ አልጋ ስለሌላት የምታድረው አፈሩ ላይ ነበር። ልብሶቿም አሮጌና የተበጫጨቁ ናቸው። ከዕለታት አንድ ቀን የሀገሪቱ ንጉስ ትልቅ ግብዣ አደረገ። የንጉሱ ልጅ የተዋበች ቆንጆ ሴት ካገኘሁ አገባለሁ በማለቱ የሀገሩ ልጃገረዶች በሙሉ የተዋበ ልብስ እየለበሱ ወደንጉሱ ግቢ ተጓዙ። የሲንድሬላ እህቶችም የተዋበ ልብስ ለብሰውና ተቆነጃጅተው ሄዱ።

«ሲንድሬላ ግን ለመሄድ አልቻለችም። ምክንያቱም ምንም ልብስ የላትም። በዚህ በጣም ስላዘነች ወደእናቷ መቃብር በመሄድ አለቀሰች። ቤት ተመልሳ ተክዛ እንደተቀመጠች ግን 'ዕድል' የምትባል ወይዘሮ በሲንድሬላ እናት መቃብር ላይ በበቀለው ዛፍ ላይ ከሚኖሩት ነጫጭ ወፎች ጋር ሆና ወደሲንድሬላ መጣች።



«ወፎቹም የያዙትን በጣም ግሩምና ልዩ ልብስ ለሲንድሬላ አለበሷት። ልብሱ በወርቅ ያጌጠ ነበር። ቀጥላም ወይዘሮ ዕድል ከመስተዋት የተሠራ በጣም የሚያብረቀርቅ ልዩ ጫማ አደረገችላት። ከዚያም በአራት ነጫጭ ፈረሶች በሚጐተት ሠረገላ ላይ አስቀመጠቻትና እንዲህ ስትል አስጠነቀቀቻት፤

«ልክ ከምሽቱ አምስት ሰዓት መሆኑን የሚያመለክተው ደወል ሲደወል በፍጥነት ወደቤትሽ ተመለሺ። ከአምስት ሰዓት አንዲት ደቂቃ ብታሳልፊ ግን ይህ ልብስ ከላይሽ በሮ ይጠፋል። እናም እንደበፊቱ ቡትቷም ስለምትሆኚ ሰዓቱን እንዳታሳልፊ። በይ አሁን ወደንጉሱ ግብዣ ሂጂ» በማለት ሸኘቻት።

«የሲንድሬላ ሠረገላ ንጉሱ ግቢ ሲደርስ ሰዉ ሁሉ እየተንጠራራ ይመለከት ጀመር። የመጣችው ሴት በጣም የተዋበች ስትሆን ቆንጆና ታይቶ የማይታወቅ ልዩ ልብስ ለብሳለች። ሰዉ ሁሉ ወጣቷ ከየት እንደመጣች ለማወቅ ፈለገ። የሲንድሬላ እህቶችም በዚች ውብት በፈሰሰባት ወጣት ሁኔታ ፈዘው ቀሩ።

«በግብዣው ቦታ በተካሄደው ዳንስና ጨዋታ ሁሉ ሲንድሬላ ተሳተፈች። የንጉሱ ልጅ ሊያገባት እንደሚፈልግ ገልፆላት አይን፣ አይኗን እያየ መልስ

ሲጠብቅ ሲንድሬላ ወይዘሮ እድል የሰጠቻትን የወርቅ ሰዓት ስትመለከት ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ቀርተዋታል:: በጣም ደንግጣ ከሠፊው አዳራሽ እየሮጠች ወጥታ ደረጃውን ስትወርድ የአንድ እግሯ ጫማ ወለቀባት:: ልታነሳው ብትፈልግ ጠፋባት:: ሰዓቱ አልፎባት እንደቀድሞዋ ከነቡትቷ እንዳትሆን ስለፈራችም ሮጣ ሠረገላዋ ላይ ወጣችና ፈረሶቹን እያስጋለበች ተፈተለከች::

«የንጉሱ ልጅ ተከትሏት ቢወጣ ያች ውብ ወጣት በአካባቢው የለችም:: በግቢው ውስጥ እየተዘዋወረ ቢፈልጋትም ሊያገኛት አልቻለም:: እያዘነ ወደ አዳራሹ ሲመለስ ደረጃው ላይ የሚያብረቀርቅ ነገር ተመለከተ:: ፈጠን ብሎ በመሄድ ሲያነሳው÷ ከሲንድሬላ እግር ወልቆ የቀረ የአንድ እግር ጫማ ኖሯል::

«አሽከሮቹን ያን ቆንጆ ጫማ አስይዞ በመላው ሀገሪቱ እየዞሩ እግሯ በጫማው ልክ የሆነች ሴት ካገኙ ወደቤተመንግሥት እንዲያመጧት አዘዘ:: አሽከሮቹም ጫማውን ይዘው በየቤቱ እየገቡ የሴቶቹን ሁሉ እግር ይለኩ ጀመር:: ነገር ግን ጫማው ለአንዷ ሲሰፋ ለሌላዋ እየጠበበ በመጨረሻ እነሲንድሬላ ቤት ደረሱና ሁለቱ የሲንድሬላ እህቶች ጫማውን ለኩት:: የነሱ ሊሆን ግን አልቻለም:: የንጉሱ አሽከሮችም የተለመደ የመጨረሻ ጥያቄያቸውን አቀረቡ::

'ሌላ ወጣት ሴት በዚህ ቤት ውስጥ የለችም?'

'እረ ከእኛ ሌላ **ማንም** የለም' አሉ የሲንድሬላ እህቶች::

'በኋላ ቢገኝ **ግን ከንጉሱ ጋር ነው የምትጣሉት፤ ወዮላችሁ!**' በማለት አሽከሮቹ ተናግረው ሊሄዱ ሲሉ **ግን ሴቶቹ ፈሩና፣**

'መኖርማ የሆነች ሴት አለች:: የንጉሱ **ግብዣ** ላይ ግን አልነበረችም:: በዚህም ላይ እንዲህ አይነት ጫማ ልታደርግ **ቀርቶ** በህልሟም እንኳን አይታ አታውቅም' አሉ::

'ግዴለም፣ የንጉሱ ትዕዛዝ ስለሆነ ትምጣና ትለካ::'

«ሲንድሬላ ተጠርታ መጣችና ጫማውን አጠለቀች:: ልኳም ሆነ:: አዲሶቹ እህቶቿና እናታቸው እየተናደዱ የንጉሱ አሽከሮች ወድቆ የተገኘውን የአንድ እግር ጫማ ባለቤት የሆነችውን ሲንድሬላን ይዘው ወደንጉሱ ዘንድ ሄዱ:: በዚህ ሁኔታ ሲንድሬላና የንጉሱ ልጅ ተጋብተው በሰላምና በደስታ ኖሩ:: እናም ልጆ

ቹቹ፣ አይዞህ፤ አሁን ያገኘሽው ጫማም የሚጠ ይሁን አይሁን ማረጋገጣችን አይቀርም» በማለት ተናገሩ።


የሲንድሬላ ታሪክ የቹቹን ትዝታ ይበልጥ ስለቀሰቀሰበት በናፍቆት ሲሰቃይና ሲያለቅስ አመሸ።

## ኩኩ መለኮቱ

ደፋሩ ቢራቢሮ «ወደመናፈሻ ቦታዎች ሄደን እነቢዛዊትን ለመፈለግ የወሩ መጨረሻ ሩቅ ስለሚሆንብን ሰው እሚሰባሰብበት ሥፍራ እየተዘዋወርን ብንፈልግ ይሻላል» በማለት ሃሳብ አቀረቡ:: እነቹቹ በሃሳቡ ስለተስማሙም የደፋሩ ቢራቢሮ የላስቲክ ጉጆ ተጠቅልሎ ለሽክም ተዘጋጀ::

ቹቹ የሚጠጉን ጫማ ካገኘ ወዲህ ናፍቆት አገርሽቶበታል:: በዚህ ላይ ከቤቱ ከወጣ ብዙ ጊዜ ስለሆነው ፊቱ መገርጣትና ፀጉሩም መንጨባረር ጀምሯል::

በጉዞ ላይ ሳሉ አሞራው አዛጋና «አሁንስ እንጀራ በወጥ አማረኝ» አለ:: የጉዳና ልጆች እናትና አባት ስለሌሏቸው ብዙውን ጊዜ እንጀራ በወጥ አይበሉም:: ደፋሩ ቢራቢሮ አሰብ አደረጉና «ዛሬ እሁድ ስለሆነ እንጀራ በወጥ ልናገኝ የምንችልበት ቦታ አለ:: በተጨማሪም ሥፍራው ብዙ ሰው የሚሰበሰብበት ስለሆነ ቹቹ በደንብ ተመልከት:: ምናልባት የቤዙን አባት ወይም እናት እናገኛቸው ይሆናል» አሉት::



«የት ነው የም[illegible] ሲል ቹቹ ጠየቀ::

«እንጀራ በወ[illegible]ት ቦታ» አለ አሞራው::

«ተከተሉ[illegible] እኔ ደፋሩ ቢራቢሮ

[illegible]ን የማበሏ እንጀራ [illegible]

[illegible]

እያሉ ሲ[illegible] ብሉዋቸው እየሳቁ ተከተሉዋቸው:: የወሰዱዋቸውም [illegible]::

«የተገ[illegible] ብዙ ነው:: ከቀናን ደግሞ እንጀራ በስጋ ወጥ እንበላለን» አሉ ደፋሩ ቢራቢሮ::

«ተገጦር ምንድነው?»

«ጉሽ ልጆቼ ፣ የኔ እንበሶች! ጅራት የላችሁም እንጂ አንበሶች ናችሁ::

ጥያቄ መጠየቅ ለህፃናት በጣም ጠቃሚ ነው። ያልገባችሁን ነገር ከመጠየቅ፣ ያሰባችሁትን ደግሞ ከመናገር ወደኋላ አትበሉ። ተዝካር ማለት ማስታወሻ ማለት ነው። አንድ ሰው የሞተበትን ጊዜ ለማስታወስ የሚደረግ ድግስ ነው» አሉናም የእንጀራ ፍትፍት ወደሚታደልበት ቦታ ሠልፍ ለመያዝ ሄዱ።

የተሰበሰቡት ችግረኞች በስነስርዓት ተቀምጠው መቀበል ሲገባቸው ሲሻሙ የሚታደለው ምግብ እመሬት ተደፋ። እመሬት የተደፋውን ቀድሞ ለማንሳት በተደረገው ግብግብም መሃል ፍትፍቱን የሚያድሉት ሴትዮ ሳይቀሩ መሬት ላይ ወደቁ። በዚህ ጊዜ ከሴትዮዋ ጋር የመጡት ወንዶች ፍትፍት ሊቀበል የተደረደረውን ለማኝና የጉዳና ተዳዳሪ በያዙት ዱላ ይነርቱት ጀመር። ደፋሩ ቢራቢሮ፣ ቱቱንና አሞራውን ይዘው ሲሸሹ አንዱ ለማኝ ወጣባቸውና የቱቱ ጆሮ ተጉዳ። ደፋሩ ቢራቢሮም ጭናቸው ላይ አስተኝተውት ደሙን በቡትቶዋቸው ይጠራርጉለት ጀመር። ይሄኔ ከቤተክርስቲያን የሚመለሱ ሰዎች ስላዩዋቸው በሀዘኔታ ሳንቲም እየጣሉላቸው አለፉ።



«እኛ ለማኝ ነን እንዴ?» አለ አሞራው።

«እኛ አልለመንም። ከመለመን ሠርቶ መብላት ነው የሚያኮራው። ነገር ግን እኔ አርጅቼያለሁ። እናንተ ደግሞ ለሥራ ገና አልደረሳችሁም። በዚህ ላይ ቹቹን አደጋ ገጥሞታል። ይህን በመመልከት ነው ሰው የረዳን። ለማንኛውም እስካሁን የተሰጠን ገንዘብ የቹቹን ጆሮ ለማሳከምና ምግብ ለመግዛት በቂ ስለሆነ እንሂድ ልጆቼ» አሉ ደፋሩ ቢራቢሮ።

የቹቹ ጆሮ ከሱቅ በተገዛ የቁስል ፕላስተር ከተለጠፈ በኋላ ምግባቸውን በልተው እንዳበቁ እየተጋገዙ የላስቲክ ጉጆዋቸውን ከቤተክርስቲያኑ አጥር ጥግ ተከሉ።

«ለመሆኑ ቹቹ» አሉ ደፋሩ ቢራቢሮ ጉጆዋቸውን ተክለው ካበቁ በኋላ፤
«ከነቤዛ ጋር ብትገናኝ እኛን እንዴት ነው የምታደርገን?»

«አብረን ከነቤዛ ጋር እንኖራለን። መጀመሪያ ግን እርስዎ ለቤዛ አባትና እናት የጊላጉን ተረት ይነግሯቸዋል» አላቸው።

«ተረት ቢል ትዝ አለኝ። ቅድም ተረት አወራላችኋለሁ አስታውሱኝ አላሉም?» አለ አሞራው።

ወዲያው ቹቹና አሞራው ደፋሩ ቢራቢሮ ስር ተሸጉጠው አይን አይናቸውን እየተመለከቱ «አውሩልን፤ አውሩልን እንጂ!» አሉዋቸው።

«አንተ በሰላም ከነቤዛ ጋር ተገናኝ እንጂ ሌላው አያሳስብም። ትንሽ የሚያሳስበው የአሞራው ጉዳይ ነው። ይህን የመሰለ ጭንቅላት ይዞ የሚያስተምረውና የሚረዳው ቢያገኝ ኖሮ ትልቅ ሰው በሆነ ነበር» ካሉ በኋላ ተመቻቹና፤

«አንድ ሀብታም ሰውዬ ባንድ መንደር ውስጥ ይኖር ነበር። በጣም ሀብታም ይሁን እንጂ ሲበዛ ገብጋባና ቀንቋና ነበር። አምስት ሳንቲም እንኳን ለድሃ መስጠት አይፈልግም። በመጨረሻ አረጀ። በአረጀና በደከመ ጊዜ ደግሞ መሞትን በጣም አድርጎ ፈራ። በዚህን ጊዜ አንድ ወታደር ወደቤቱ መጣ። ሀብታሙ ሰውዬም ትንሽ ገንዘብ ለወታደሩ ሰጠውና እንዲህ አለው 'በሞትኩኝ ጊዜ መቃብሬን ጠብቅልኝ።'

«ብዙም ሳይቆይ ሀብታሙ ሽማግሌ ሞተና ተቀበረ:: ወታደሩም በገባው ቃል መሠረት የሀብታሙን ሽማግሌ የመቃብር ቦታ ይጠብቅ ጀመር:: በመሸ ጊዜም ሰይጣን መጣና ወታደሩን እንዲህ አለው፣

'ይህ ሽማግሌ በህይወት በነበረ ጊዜ መጥፎ ሰው ነበር:: ስለሆነም አውጥቼ ልወስደው መጥቻለሁ::'

'አይሆንም፤ ይህን ሰው አትወስደውም:: እኔ እንደሆንኩ አልፈራሁም፣ ጥፋ ከዚህ!' አለው ወታደሩ::

'ገንዘብ ልሰጥህ እችላለሁ' አለ ሰይጣኑ መልሶ::

'በጣም ጥሩ፤ ነገር ግን በጣም ብዙ ገንዘብ ነው የምፈልገው፣ ማለትም ይህን ጫማዬን መሙላት የሚችል' በማለት ጫማውን አውልቆ ለሰይጣኑ አሳየው:: ሰይጣኑም ገንዘብ ለማምጣት ባካባቢው ወዳሉ ሀብታሞች ዘንድ ሄደ:: ሰይጣኑ እንደሄደለት ወታደሩ የጫማውን ሶል ገንጥሎ ጉድጓድ ቆፈረና ጫማውን ጉድጓዱ አፍ ላይ አስቀመጠው::

«ሰይጣኑም በቦርሳ ሙሉ ወርቅ ይዞ መጣ::

'ጫማው ውስጥ ዘርግፈው' አለ ወታደሩ:: ሰይጣኑም ወርቁን ዘረገፈው:: ነገር ግን ጫማው አልሞላም::

'ይህ በቂ አይደለም:: ጨምር' አለ ወታደሩ:: ሰይጣኑም እንደገና ሄደና በትልቅ ቦርሳ ሙሉ ወርቅ አምጥቶ ጫማው ውስጥ ገለበጠ::ጫማው አሁንም አልሞላም::

'እግርህ በጣም ትልቅ ነው እንዴ? ' አለ ሰይጣኑ:: ወታደሩም ትልቁን የሰይጣን እግር አየና፣

'ትልቅ ቢሆንም ካንተ አካፋ እግር አይበልጥም!' አሁን ጭቅጭቁን ትተህ ጫማውን በወርቅ ሙላ' አለው::'

«ሰይጣኑም ለሦስተኛ ጊዜ ሄደ:: ከብዙ ቆይታ በኋላ እጅግ በጣም ትልቅ በሆነ ቦርሳ ሙሉ ወርቅ ይዞ ተመለሰና ጫማው ውስጥ ገለበጠው:: አሁንም ጫማው አልሞላም::



«በዚህን ጊዜ ሰይጣኑ በጣም ተቆጣ። አይኖቹ ቀሉ፣ ቀንዱ ቆመ፣ ጭራውንም ቀሰረ። ጥፍራም እጆቹን ወደወታደሩ ሰድዶ ሊያንቀው ሲል ግን ፀሀይ ወጣች። ሰይጣኑም ብርሃን ስለሚፈራ ሸሽና ጠፋ።

«ወታደሩ እየሳቀ ወርቁን በሙሉ አውጥቶ ለድሆች አከፋፈለ። በመጨረሻም ለራሱ ጥቂት ይዞ ወደቤቱ ሲሄድ እንዲህ አለ 'በደስታ ለመኖር ይኼ በቂ ነው!' ብለው ተረታቸውን ጨረሱ ደፋሩ ቢራቢሮ።

«ወታደሩ ጉበዝ ነው» አለ ቹቹ።

«እንዴት?» አሉ

«ሰይጣኑን አልፈራውም፥ ደግሞ የአገኘውን ወርቅ ሁሉ አልወሰደም፤ ለድሆች አከፋፈለ። የቤዞ እናትም ሁልጊዜ ተካፍሎ መብላት ያስፈልጋል። ተካፍሎ መኖር ፍቅር ነው ትላለች» አላቸው።

«እውነቷን ነው፥ ተገቢ አባባል ነው» አሉ ደፋሩ ቢራቢሮም በበኩላቸው።

«አባባ ደፋሩ ቢራቢሮ፥ የእርስ ተረት በሙሉ ስለሀብታምና ድሀ ብቻ ነው:: ሀብታሞችን ይጠላሉ እንዴ?» በማለት አሞራው ጠየቃቸው::

«ድንቅ ጥያቄ ነው?» አሉ ጢማቸውን እያሻሹ፡ «አየህ አሞራው፥ ሀብታሞች ቢተባበሩ እንደ አንተ እናትና አባቱ የሞቱበትን፣ እንደ ሃምሣ እግር አባትና እናቱ በጦርነት ያለቁበትን፣ እንደእኔ አርጅተው መውደቂያ ያጡትን፣ እንደቹቹ ቤቱ ጠፍቶበት ውጭ የቀረውንና በተለያየ ምክንያት ጉዳና ላይ የምንኖረውን ሊረዱንና ሊደግፉን ይችሉ ነበር:: ግን ተመልከት» አሉት ወደመቃብሩ ሥፍራ እያመለከቱ:: «ከሞቱ በኋላ እንኳን ለኛ የማይረባ ፍትፍት እየሰጡ ሐውልታቸውን በብረትና በድንጋይ ይሰራሉ:: ተነስተው አያዩት?! እኛ ግን ይኸው ሳንሞት በላስቲክ ቤት ውስጥ እንኖራለን:: ቹቹ የቤዛ እናት ተናገረች እንዳልከው ተካፍሎ መብላት እንጀራንና ዳቦን ብቻ አይደለም:: አብረን በዚህች ምድር ላይ የምንኖር ከሆነ መረዳዳት አለብን:: ሀብታም ስለሆኑ አልጠላቸውም:: ነገር ግን ድርጊታቸው ያጠላኛል:: እስቲ ይሆን በምሳሌ ላስረዳችሁ:: ለምንድነው ቹቹ ክፉንችላን የጠላው? ክፉንችላ ለጠላው ስላላደደው ነው:: ሊበላው ባይፈልግ፥ እንደጉፌር ቢረዳው ኖሮ አይጠላውም ነበር:: እንግዲህ ቹቹ ጉፌርን ሲወድ፣ ክፉንችላን የጠላው በድርጊቱ ነው እንጂ ሁለቱም እኮ ያው ውሾች ናቸው» በማለት ተንትነው አስረዱዋቸው::

ከዚያም ትንሽ አረፍ እንዳሉ፣«ተነሱ እስቲ ልጆች፣ የቹቹን ቤተሰብ ለማግኘት ስንጥር እግዚአብሔር እንዲረዳን ሄደን እንለምነው» በማለት ወደቤተክርስቲያኑ ግቢ ይዘዋቸው ገቡ::

ዘጠኝ ሰዓት ስለሆነ የቤተክርስቲያኑ ግቢ ፀጥ፣ ረጭ ብሏል:: አልፎ አልፎ በየዛፉ ስር ለየብቻ ቆመው የሚፀልዩ ሰዎች ይታያሉ:: ቤተክርስቲያኑ ግቢ አስፋልት ላይ ርግቦች ጥራጥሬ ይለቃቅማሉ::

የቤተክርስቲያኑን ደረጃ ወጥተው ግቢውን ሲያቋርጡ ቹቹ እየፈነጠዘ፣ «ኩኩ መለኮቴ! ኩኩ መለኮቴ ያቻትና» አለ:: ከዚያም አጭር ቃጪት ሲያሰማ ፈንጠር ብላ ጥሬ ትለቅም የነበረች ደረቷ ላይ ጥቁር የጣለባት ርግብ ወደሱ በራ መጣች::

## ታላቅ ተስፋ

«ለተወደዳችሁና ለተከበራችሁ የቤዘ አባትና እናት፥ እንዲሁም በጣም ለማፈቅራችሁና ሁልጊዜም ለማስባችሁ ለቤዝዬና ለሚጥዬ፤ እንደምናችሁ? ደህና ናችሁ ወይ?

«ከተለያየንበት ቀን ጀምሮ ሳላስባችሁ ቀርቼ አላውቅም:: ወደእናንተ ዘንድ ተመልሼ ከብሬዎችሁ መዝሙር እየዘመርኩ፣ ድብብቆሽ እየተጫወትኩና፣ ቤዝዬ የከበደሽን ትምህርት እያስጠናሁሽ ለመኖር እፈልጋለሁ:: የጉዳና ተዳዳሪ በመሆኔ በጣም ነው የተሰቃየሁት:: እባክሽ ቤዝዬ ለእናትና ለአባትሽ ንገሪልኝና ወደቤት ልመለስ:: እዚህ የሚበላ፣ የሚጠጣ የለም፤ ማደሪያ ቤትም የለም:: በየመንገዱና በየበረንዳው ነው የማድረው:: ልብሴ አልቆብኛል፣ ጫማም የለኝም:: ብርድ፣ ፀሀይ፣ ዝናብ አሰቃይቶኛል:: ስለዚህ እባክሽን ወደአንቺ እንድመጣ ለእናትና ለአባትሽ ንገሪልኝ::

«የቤዘ አባትና እናትም እባካችሁ የጉዳና ተዳዳሪ ሆኜ እንዳልቀር እርዱኝ:: እኔ'ኮ የሚናገር፣ የሚራመድ፣ የሚጫወት አሻንጉሊት እንጂ ሰይጣን አይደለሁም:: ለቤዘ የተሰራሁ አሻንጉሊት ነኝ:: እዚህ ያሉ የጉዳና ተዳዳሪ ህፃናት እንደሚሉኝ ዱርዬ አሻንጉሊት ሆኜ ለመቅረት አልፈልግምና ቶሎ ወደቤት መልሱኝ:: አባባ ደፋሩ ቢራቢሮና አሞራው የተባሉት ጓደኞቼ ሰላምታ ያቀርቡ ላችኋል:: በሰላም ለመገናኘት ያብቃን::

የቤዝዬ አሻንጉሊት፣ ቹቹ»

ቹቹ ይህን ደብዳቤ ፅፎ ለደፋሩ ቢራቢሮና ለአሞራው አነበበላቸውና እንዲላክ ተስማሙ:: ከዚያም ኩኩ መለኮቱ እግር ላይ አስሩትና ለቀቁት::



ኩኩ መለኮቴም በዛፎቹ አናት ላይ በርራ ስትሄድ አምራው፣ ደፋሩ ቢራቢሮና ቹቹ ተመልክተው ደስ አላቸው::

«ጉድ ሆነናል! ጉድ! አይ አለመማከር፤ በቃ የደብዳቤው ነገር ዋጋም የለው:: አሄሄ!» እያሉ ደፋሩ ቢራቢሮ በቁጭት አጨበጨቡና፣ ጭንቅላታቸውን በሁለት እጆቻቸው ይዘው ቁጢጥ አሉ:: አምራውና ቹቹም ደንግጠው አጠገባቸው ተገትረው ቀሩ::

ቆይቶ አምራው እንዲህ አለ፣ «ደብዳቤው ምን ሆነ ነው የሚሉት? ምንድነው ያልተማከርነው?»

«አይ አምራው፣ ተወው! ተወው! የኔ ነው ጥፋቱ፤ የኔው የሽማግሌው ጭንቅላት ነው ጥፋቱን የሠራውና እናንተንም ያሳሳታችሁ» አሉ በሀዘን::

«እኮ ምንድነው ያጠፉት? ይንገሩን እንጂ» በማለት አምራው ውጥር አድርጐ ያዛቸው:: ቹቹ ግን በኩኩ መለኮቴ በኩል የላከው ደብዳቤ ለነቤዞ

እንደሚደርስ እርግጠኛ ሆኗል:: ኩኩ መለኮቴ እንደሆነ በርራ ሄዳ የምታርፈው እቤቷ ነው ሲል አሰበ:: ነገር ግን ፍርሃት ደግሞ ተሰማው:: እናም፣

«ደብዳቤው ምን ሆኗል?» ሲል በፍርሃት ጠየቀ::

«አያችሁ ልጆቼ፣ ኩኩ መለኮቴ ቤቷ ደርሳ ታርፋለች:: ከዚያም አንድ ሰው እግሯ ላይ ወረቀት እንዳለ ይመለከትና ፈትቶ ያነበዋል:: ከቹቹ ለቤዛ የተፃፈ ደብዳቤ መሆኑን ሲያውቅ በቀጥታ ለቤዛ አባትና እናት ይሰጥና አንተ እንደላከው ያውቃሉ:: ትልቁ ጥፋት ይህ ደብዳቤ ከየት እንደተላከ የቤዛ ወላጆች ሲያውቁ አለመቻላቸው ነው» አሉ::

«ከኔ ከቹቹ ነዋ የተላከው:: ስሜን እኮ ከደብዳቤው ስር ፅፌበታለሁ::»

«እሱማ ፅፈኸዋል፤ ልክ ነህ:: ነገር ግን የላኪው ስም ብቻ ሳይሆን አድራሻህ ጭምር ነበር መፃፍ ያለበት:: የቤትህን ቁጥር ወይም የስልክ ቁጥርህን ብታውቅ ኖሮ በዚያ አድራሻ ፈልገን ወይ ስልክ ደውለን እናገኛቸው ነበር:: ያን ባለማወቅህ ይኸው ትንከራተታለህ:: በኩኩ መለኮቴ በኩል ደብዳቤ ስትፅፍ ደግሞ የት እንደምትገኝ፣ ማለት የቤተክርስቲያኑን ስምና የሠፈሩን ስም ብንፅፍበት ኖሮ የቤዛ አባቷም ሆነ የቤዛ እናት ቤዛን ይዘው ቀጥታ እዚህ ይመጡና ትገናኙ ነበር:: ያጠፋሁት እኔ ነኝ:: መቸኮል አልነበረብኝም:: ያንተና የቤዛ መገናኘት በጣም ስለአጓጓኝ ተቻኩዬ ስህተት ሰራሁ:: ልጄ ቹቹ ይቅርታ አድርግልኝ እባክህ» ሲሉ አዝነው ለመኑት::

ቹቹ ለሁለተኛ ጊዜ በፈፀመው ስህተት በጣም አዘነ:: አሞራውም ቢሆን በጣም አዝኗል:: ምክንያቱም ቹቹ ከነቤዛ ከተገናኘ የቤዛ አባትንና እናትን ቹቹ ለምኖለት አብሮ ለመኖር ተመኝቶ ነበር:: አሁን ግን ኩኩ መለኮቴ የወሰደችው ደብዳቤ ለነቤዛ ቢደርስም ቹቹ የት ሆኖ እንደላከው ስለማያውቁ አያገኟቸውም::

ከብዙ ዝምታ በኋላ «ለማንኛውም ኩኩ መለኮቴን እንድናገኝ ለረዳን አምላክ ፀሎት ማድረስ ተገቢ ነውና ፀሎታችንን እናድርስ፤ እግዚአብሔር ይረዳናል» በማለት ደፋሩ ቢራቢሮ ተናግረው ለጥቂት ጊዜ ጸለዩ:: «እግዚአብሔር ሆይ፣ ቹቹን በሰላም ከነቤዛ ጋር አገናኝልን» ሲሉ ነበር ሁሉም የፀለዩት:: ከፀሎት በኋላ ላስቲክ ጉጆዋቸው ውስጥ ገብተው በፀጥታ ተቀመጡ::

ቀኑም ቀስ በቀስ መሸና ፀሀይ ጠልቃ ጨለማ ሆኑ:: ወደደፋሩ ቢራቢሮ የላስቲክ ቤት የሚገባው ብርሃን በርቀት ካለው የመንገድ መብራትና ከሚተላለፉት መኪኖች የሚመጣ ነው::

ሁሉም በሀዘን ስለተዋጡ የሚናገር ጠፋ:: መቼም ህፃናት ሲያዝኑ ማጫወት የአዋቂዎች ስራ በመሆኑ፣ ደፋሩ ቢራቢሮ ቀስ አሉና «ልጆች ተረት ላውራላችሁ?» ሲሉ ጠየቁ:: አሁን፣ አሁን ቹቹ ከቤዙና ከሚጡ ጋር ከተገናኘሁኝ አወራላችዋለሁ በማለት ተረት መሰብሰብ በጣም ፈልጓል:: አሞራው ደግሞ ተረት ሲወራለት ደስ ብሎት እንቅልፍ ስለሚወስደው «እሺ አውሩልን» በማለት በአንድነት መለሱ::


ደፋሩ ቢራቢሮ ጉሮሯቸውን «እህህ!» በማለት አፀዳዱና ቡትቷቸውን ወደ ትከሻቸው ከፍ አድርገው ሲያበቁ ተረቱን ጀመሩ::

«ከቡችልነቱ ጀምሮ በአንድ ገበሬ ቤት ውስጥ ያደገ አንድ ውሻ ነበር:: ገና ቡችላ ሳለ የገበሬውን ትናንሽ ልጆች እያጫወተ፣ አብሮዋቸው እየሮጠ፣ ጨርቅ ኳላቸውም ርቃ ስትሄድ በአፉ በማምጣት ያገለግላቸው ነበር:: ቀስበቀስ እያደገ ሲሄድም የሚኖርበትን ገበሬ ቤት ከሌባና ከአውሬ መጠበቅ ጀመረ::

«ቀን ቀን በጉቹ ሜዳ ላይ ሳር ሲግጡና ውሃ ሲጠጡ፣ ከቀበሮና ከተኩላ ይጠብቃቸዋል:: ፀሀይ ለመጥለቅ ስትቃረብ ደግሞ ከግራና ከቀኝ እንዲሁም ከኋላ በመዘዋወር በጉቹ መንገዳቸውን እንዳይስቱ እየነዳ ወደቤት ይመልሳቸዋል::

«ሌሊት ሲሆን ደግሞ ዶሮዎቹን ሸለምጥማጥ፣ አህዮቹን ጅብ፣ በጉቹን ቀበሮና ተኩላ እንዳይበሏቸው ግቢውን እየዞረ ይጠብቃል::

«እንዲህ እንዲህ እያለ ሲሰራ ይኸ ሁኔታው ከሁሉ የበለጠ ቀበሮና ተኩላን አስቀየማቸው:: 'እንዴት የኛው አይነት ፍጥረት ሆኖ ሳለ በግ እንኳን እንዳንሰርቅ ያደርገናል?' በማለት ተነጋገሩ::



«ቀበሮና ተኩላ ቀን፣ ቀን በጉቹን ከሚጠብቅበት ሜዳ ድረስ እየመጡ 'መልክህ ሁሉ የኛን ይመስላል። እስቲ ጭራህን፣ ጥርስህን፣ አይንና አፍንጫህን ተመልከት። እስቲ የእግር ጣትህን እየው፣ ሁሉም ነገርህ የኛ አይነት ነው። ታዲያ እንዴት በኛ በወገኖችህ ላይ ትጨክናለህ? ኧረ ተው። ምን አለበት አንድ በግ እንኳን ብትሰጠን፣ ወይ ስርቀን ስንወስድ ዝም ብትለን?' እያሉ ይለምኑታል።

«ውሻውም፣ 'በርግጥ ሁሉ ነገራችን አንድ አይነት ነው። ሁሉንም ተመልክቼዋለሁ። ነገር ግን ሥራችን አይመሳሰልም። እኔ ሰርቼ እበላለሁ እናንተ ግን በማጭበርበር፣ በማታለልና በመስረቅ ትኖራላችሁ። ስርቃችሁ ብሉ፣ ሌብነትና ማታለል አይጠቅማችሁም። ሂዱ እግዜር ለእናንተ ያሰናዳቸው ድኩላና ሚዳቋ ጫካ ውስጥ አሉላችሁ' እያለ ይመልሳቸው ነበር።

«ይኸው ውሻ ቀን፣ ቀን በእረኝነት፤ ሌሊት፣ ሌሊት ደግሞ በዘበኝነት ያለማቋረጥ ለረዥም አመታት ሲሰራ ኖረ። ቀስ በቀስ ግን አዳዲስ ከተወለዱ በጉችና ፍየሎች ጋር መሮጥና መጠበቅ እያቃተው መጣ። ሁኔታውን የተመለከተው ገበሬም ውሻውን ቤት እንዲውል አድርጎ እረኛ በመቅጠር በጉችን ሲያስጠብቅ፣ ሌሊት ሌሊት ግን ግቢውን የሚጠብቀው ይኸው ውሻ ነበር። እንደልቡ ተሯሩጦ ግቢውን መጠበቅ ቢያቅተውም በአይኑ ከማየት ይልቅ በአፍንጫው በማሽተት የተከላ፣ የቀበሮ፣ የሸለምጥማጥና የጅብም ሆነ የሌባ ጠረን ሲሸትተው በመጮህ ገበሬው እንዲነቃ ማድረጉን አልቀረም።

«ቀስ በቀስ ግን ድምፁ ደከመበት፣ መተኛትም አበዛ። መሮጥ ቀርቶ መራመድ እንኳን አቃተው።

«ከዕለታት አንድ ቀን ማታ ገበሬው ወደቤቱ ሲገባ፣ ይኸን ውሻ በሩ ላይ ተኝቶ አየው። ፀጉሩ ከላዩ ላይ መርገፍ ጀምሯል። አይኑ ሞጭሙጮ ሞራ ለብሷል። እግሩም ተወለጋግዷል። ደስ የሚል ፀጉራም ጭራው በጭቃና በቆሻሻ ተለውሶ እንደዱሮው ጌታው ሲመጣ ወዲያና ወዲህ ማለቱን ትቷል። ዝንቦችም ውሻው ላይ ያለውን ቆሻሻ ስለሚወዱ ወረውታል።

«ጠንካራና ወጣት ሳለ በአፉ የሚይዛቸው፣ በእግሩ መትቶ የሚገድላቸው ዝንቦች ዛሬ አይኑን ወረውና አፉ ላይ ተሰባስበው እያየ እግሩን አንስቶ ቀርቶ ጭንቅላቱን እንኳን በማነቃነቅ ከላዩ ማባረር አቅቶት ተመለከተ። ገበሬውም ወደቤቱ ገብቶ ሚስቱን፣

'ይሄ ውሻ በጣም አርጅቷል። ስለዚህ ገመድ አዘጋጅተሽ ጠብቂኝ። ጉትቼ ወስጄ ገደል እጥለዋለሁ' አላት። ይህንንም ያ የደከመና ያረጀ ውሻ ሰማና በጣም አዘነ። ወደጓሮም ሄዶ አለቀሰ። የዚህን ጊዜ አንድ ወጣት ቀበሮ አየውና፣ 'ምን ሆንክ?' በማለት ጠየቀው።

«ውሻውም 'ከልጅነቴ ጀምሮ እዚህ ግቢ ውስጥ ነው የኖርኩት። የገበሬውን ልጆች ሳጫውት፣ ቀን ቀን በጉችና ፍየሎች ሳግድ፤ ሌሊት ደግሞ ሌባ እንዳይገባና አውሬ እንዳይመጣ ስጠብቅ፤ ጉልበቴን ሳልቆጥብ ሳገለግል ቆየሁኝ። አሁን ግን ማርጀቴን አይቶ ገደል ወስዶ ሊጥለኝ ገመድ እንድታዘጋጅለት ሚስቱን

ሲያዝ ሰምቼ ነው የማለቅሰው' ሲል ለወጣቱ ቀበሮ ነገረው::

«ይህ ቀበሮ ጫካ ውስጥ የሚገኙ እንስሳትን እያደነ የሚበላ እንጂ የሰው ንብረት የማይነካ ነበር::

'አይዞህ፣ ነገ ጠዋት እመጣና ከሞት አድንሃለሁ' አለው::

'እንዴት አድርገህ ታድነኛለህ? እንዲያውም በጉቹን ልትበላ የመጣህ መስሎት አንተኑ እንዳይገልህ:: ይቅርብህ አትምጣ' አለው::

'የለም አይገለኝም:: ይልቅ ስማ፣ ገበሬው ልጅ ወልዷል አይደል?' ሲል ጠየቀው::

'አዎን፣ ምነው?' አለ ሽማግሌው ውሻ::

'ህፃኑ ጠንካራ እንዲሆን እናቱ ጠዋት፣ ጠዋት ፀሀይ ልታሞቀው ታወጣው የለ? '

'አዎን::'

'እሱን ይዤው እሄዳለሁ' አለ ወጣቱ ቀበሮ::

'እንዴ አይሆንም! ምን ማለትህ ነው? እኔን ለማዳን ህፃኑ ምን ያደርግልሃል?'

'የህፃኑን ልብስ ከሼ እይዝና ቀስ እያልኩ እሮጣለሁ:: ያኔ አንተ የተቻለህን ያህል ጮሀና እያደንገህ ወደኔ ሩጥ:: ሰዎቹ ህፃኑን ይዤ አንተ ስታባርረኝ ሲመለከቱ ህፃን ልጃቸውን እንዳዳንክላቸው ይረዳል:: እኔም አንተን የፈራሁ መስዬ ልጁን በመጣል ወደ ጫካ እሮጣለሁ' ሲል አስረዳው::

'ይገርማል፣ ምንም ጥሩ ነገር ሳላደርግልህ እንዴት ልትረዳኝ ፈለግህ? ' አለ ውሻው::

'አታስታውስም እንጂ በጣም ትልቅ ውለታ ነው የዋልክልኝ::'

'እንዴት? የት ነው ደግሞ ጥሩ የዋልኩልህ? እስከማውቀው ድረስ ለአባትህ ቀበሮም ሆነ ለአጐትህ ተኩላ አንድ በግ እንኳን እንዲወስዱ አልፈቀድኩላቸውም::'

'የለም፣ ድሮ አባቴ ቀበሮና አጐቴ ተኩላ እየመጡ ሲለምኑህ፣ 'የሰው ንብረት አልሰጥም፣ ሰርታችሁ ብሉ፤ ለእናንተ የሚሆን ሚዳቋና ድኩላ እግዜር

ፈጥሮላችኋል' በማለት መከረኋቸው ነበር:: እኔ ያን ምክር ተጠቅሜ ወዲያው ወደሜካ ተመለስኩ::

'አባቴን ግን በግ ሊሰርቅ ሲል ገበሬው በጥይት ገደለው:: አጐቴ ተኩላም ፍየል ሊሰርቅ ሲሄድ በሳር በተሸፈነ ወጥመድ ተያዘና ሰዎች ደብድበው ገደሉት:: እኔ ግን ይኸው ባንተ ምክር መሠረት ስርቄ ስለኖርኩ በህይወት ተገኘቼ ያንተንም ውለታ ለመመለስ በቃሁ' አለውና ተለያዩ::

«ጠዋት የገበሬው ሚስት ህፃን ልጁዋን ለሌን አንጥፋ ፀሀይ እንዲሞቅም በዚያ ላይ አስተኝታው ለገበሬው ገመድ ልትፈልግ ወደቤቷ ገባች:: የዚህን ጊዜ በምክራቸው መሰረት ወጣቱ ቀበሮ ህፃኑን ይዞ ሲሄድ፣ አሮጌው ውሻ እየተንገዳገደ በመሮጥ በአረጀ ድምፁ ጮኸ:: የህፃኑን ለቅሶና የውሻውን ጩኸት የሰሙት ገበሬና ሚስቱ ወደውጭ ሲወጡ፣ ልጃቸውን ቀበሮ ይዞት ሲሄድ፣ ውሻው ደግሞ ሲያባርረው ተመለከቱና ልጁን ለማስጣል ወደቀበሮው ሮጡ:: ቀበሮውም በተናገረው መሠረት ህፃኑን ጥሎ ወደሜካው ገባ::

«ገበሬውም አሮጌው ውሻ ህፃን ልጁን ስለአዳነለት በጣም በመደሰት ውሻውን አቅፎ ካመሰገነው በኋላ በሳሙናና በውሃ አጠበው:: ከዚያም እቤት ውስጥ አሮጌ ልብሶቹን በማንጠፍ አስተኝቶት ጥሩ ምግብ እየሰጠ እስከዕለተ ሞቱ ድረስ አኖረው ይባላል:: ስለዚህ ልጆች ጥሩ ሥራ ከሠራችሁ ፣ ጥሩ ነገር ታገኛላችሁ» በማለት ደፋሩ ቢራቢሮ ተረታቸውን አበቁ::

«ፓ!፣ በጣም ደስ የሚል ተረት ነው» አለ አሞራው::

«እኔን ደግሞ ይሄ ተረት ያን ደግ ውሻ ጐፈርን አስታወሰኝ» አለ ቹቹ::

በዚህ ጊዜ የቹቹን ጠረን እያገኘ፣ እንደገና እየጠፋበት በአካባቢው ይዘዋወር የነበረው ጐፈር ድምፁን ሲሰማ፣

«እንዴ ቹቹ! እዚህ ምን ታደርጋለህ? እኔ'ኮ ጠረንህን ተከትዬ ነው የመጣሁት:: መልክህን እስካይ ወይም ድምፅህን እስክሰማም ነበር የጠበቅኩት» በማለት የላስቲክ ጐጆዋን በር ገለጥ አድርጎ ብቅ አለ::

«ጉፈር! ጉፈር!» በማለት ቹቹ ጮኸና በአምራውና በደፋሩ ቢራቢሮ ላይ ተረማምዶ ጉፈር አንገት ላይ ተጠመጠመ::



«ምን ታደርጋለህ እዚህ? የትስ ጠፍተህ ነበር?» ሲል ቹቹ ጠየቀው::

«ምን ማለትህ ነው? መጀመሪያ ቀን እኔና አንተ የተገናኘነው እዚያ መንገድ ላይ ነው:: ያኔ አንተ ከተማውን በደንብ አታውቀውም:: እኔ ግን ከዱሮ ጀምሬ እዚህ ቤተክርስቲያን ጥግ ነው የማድረው:: ሰሞኑን ጠረንህን ተከትዬ መጣሁና ድምፅህን እስክሰማ በመጠበቅ አገኘሁህ:: ደህና ነህ? አሁንም ከቤተሰቦችህ ጋ አልተገናኘህም?»በማለት ጉፈር ጠየቀው:: «ያን ጊዜ ቤዙ ያቻትና ብለህ የሮጥከው ሳታያት ነው እንዴ?» ሲል ጉፈር ጠየቀው::

«የተሳሳትኩት 'ኮ የቤዙን ዓይነት ምልክት ያለበት ቦርሳ በማየቴ ነው:: አንተስ ከፉንቾላን አገኘኸው?»

«ከእንግዲህ የሚያስፈራህ ነገር የለም፣ ክፋንችላ እንደሆነ ሞቷል» አለው ጉፈር።

«ምን ሆኖ?»

«አንተን ሲያባርር ከግንብ ጋር ተጋጭቶ ወድቆ አልነበረም? ያኔ ታዲያ በጣም አሞት መሬት ላይ እየተንደባለለና ከፍተኛ ድምፅ እያሰማ የግቢውን ዘበኛ ስለረበሸው በዱላ ደብድቦ ገደለው» አለ።

የክፋንችላን ሁኔታ ቹቹ ለደፋሩ ቢራቢሮ ዘርዝሮ አጫውቷቸው ስለነበር። «ይኸው ነው የክፉ ስራ መጨረሻው» አሉና «ግባ ጉፈር፣ ግባ የኔ ጠጉራም፣ በመካከላችን ፍቅር ካለ የኔ የላስቲክ ጉጆ በቂ ናት» አሉት።

ጉፈር፣ ቹቹ፣ አሞራውና ደፋሩ ቢራቢሮ በላስቲክ ጉጆ ውስጥ ተሰባሰበው ሳሉ ደፋሩ ቢራቢሮ እንዲህ አሉ፣ «ልጆች፣ እንግዲህ እነሆ ቹቹና ጉፈር ተገናኙ። ቤዙና ቹቹን ደግሞ እንድናገኝ ፈጣሪ ይርዳን፤ እንተኛ» አሉ።

«አሜን፣ ፈጣሪ ይርዳን» አሉና አራቱም በየአቅጣጫው ተኙ።

* * *

ሁሌ ማለዳ መነሳት የምትወደው የቤዛዊት ጓደኛ ሶስና፣ ኩኩ መለኮቴ እግር ላይ ወረቀት ተንጠልጥሎ አየች። ባለመደቻት ዓይነት ሁለቴ ስታፏጭም ርግቧ መጥታ የዘረጋችላት እጅ ላይ አረፈች። ሶስናም የታሰረውን ወረቀት ከኩኩ መለኮቴ እግር ላይ ፈትታ ስታነበው ከቹቹ የተጻፈ መሆኑን ተረዳች። ቤዛዊትና ሶስና ጓደኛሞች ስለሆኑና ስለቹቹ ብዙ ነገር ታውቅ ስለነበር፣ ወደነቤዛዊት ቤት በሩጫ ሄዳ ለቤዛዊት አባት ደብዳቤውን ሰጠችው።

ደብዳቤው ከተነበበ በኋላ ቹቹ ከጠፋ ጀምሮ መሳቅ፣ መጫወትና እንደዱሮው መብላትና መጠጣት ትታ የነበረችው ቤዛዊት በጣም ተደስታ ከአንዱ ክፍል ወደሌላው እየሮጠች፣ «እልል በሉ! እልል በሉ! ቹቹ ተገኘ!» ስትል ኮስና እና ሚጡም እሷን ተከትለው፣ «እልል በሉ ቹቹ ተገኘ! እልል በሉ ቹቹ ተገኘ!» በማለት ደስታቸውን ገለፁ።

የቤዛዊት አባትም በድጋሚ ድምፁን ከፍ አድርጎ ደብዳቤውን አነበበ። የቤዛዊት እናት እንደልማዷ የተለየ ነገር በማስተዋሏ፣

«ምን ዋጋ አለው!» አለች:: «ደብዳቤው የተፃፈበት ቀንና ከየት እንደተላከ አይታወቅም'ኮ!»

በዚህ ንግግር የቤዛዊት አባት ተደናግጦ ደብዳቤውን እያገላበጠ ቢመለከት አድራሻም ሆነ የተፃፈበትን ቀን የሚገልፅ ምንም ፅሁፍ የለም:: በዚህም በጣም አዘነ:: በእናቷ ንግግር ወዲያውኑ ተስፋ የቆረጠችው ቤዛዊት ቹቹ እንደገና የማይገኝ መሆኑ ተሰምቷት «በቃ ቹቹ አልተገኘም ማለት ነው?» በማለት ተናግራ ስቅስቅ ብላ ስታለቅስ ሚጡና ሶስናም አብረዋት አለቀሱ:: ሊካም «ሚያው! ሚያው! ሚያው!» በማለት ጮኸች:: ቤቱ በሀዘኔቱ ለቅሶ ተተራመሰ:: የቤዛዊት አባት በጣም ስለአዘነ እንባ አቀረረ::

ሁኔታው ከደስታ ወደሀዘን ሲለወጥ፣ የቤዛዊት እናት መልሳ «ትናንት ዝናብ አልዘነበም፤ ዛሬም ዝናብ አልዘነበም:: ስለዚህ ደብዳቤው የተፃፈው ትናንትና ነው:: ከትናንትና በፊት ባሉት ቀናት የተፃፈ ቢሆን ዝናብ ስለሚመታው ረጥቦ ከኩኩ መለኮቴ እግር ላይ ይጠፋ ነበር» አለችና ትንሽ ስታስብ ቆየች::

ድንገት ደግሞ «እልል በሉ! እልል በሉ! ቹቹን እናገኘዋለን፤ እልል በሉ!» በማለት የደስታ እንባ እየወረዳት እየሳቀችና እያለቀሰች ንግግሯን ቀጠለች:: ሌሎቹ በሁኔታዋ ተገርመው ያዩዋታል::

«እግዚአብሄር ይመስገን፤ የሽርሽር ፕሮግራማችን እንደገና ይጀምራል:: ቹቹና የቹቹ ጓደኞችም ከኛ ጋር ይኖራሉ:: የቤዙ አባትም የጉዳና ተዳዳሪ ልጆችን ለመርዳት በተቋቋመው ማህበር ውስጥ እመዘገባለሁ ያልከውን አትርሳ:: ልጆች እግዚአብሄርን አመስግኑ፤ እልል በሉ! እልልልልል!» አለች::

አሁንም የቤዛዊት አባት፣ ቤዛዊት፣ ሶስና እና ሚጡ ተገርመው ያዩዋታል::

«ቹቹ የት እንዳለ አውቄአለሁ:: ኩኩ መለኮቱ ሁሌ የምትሄደው ከኛ ቀበሌ ጉን ወዳለው ቤተክርስቲያን ነው:: እዚያ ሁሌ ጥራጥሬ ስትለቅም አያታለሁ:: ኑ፣ አሁኑኑ በጠዋት እንሂድ!» አለች::

«አዎን፣ ኩኩ መለኮቴ ሁሌ እዚያ ቤተክርስቲያን ነው የምትሄደው፡፡ የቤዛ እናት ልክ ነሽ» አለች ሶስና፡፡

ጊዜ ሳያጠፉ የቤዛዊት አባት፣ የቤዛዊት እናት፣ ቤዛዊት፣ ሚጡና ሶስና ኩኩ መለኮቴ ወደምትገኝበት ቤተክርስቲያን በጥድፊያ ተጓዙ፡፡

# እርካታ

ጠዋት ቹቹ፣ ጉፈርና ደፋሩ ቢራቢሮ ከዕንቅልፋቸው እንደነቁ አሞራው እንዲህ አለ፤

«አባባ ደፋሩ ቢራቢሮ ለምን ቤተክርስቲያን ገብተን ኩኩ መለኮቴን እንፈልጋትም? ቢድጋሚ ካገኘናት አድራሻ ያለው ደብዳቤ ልፈን እንለቃታለን።»

«ተባረክ ልጄ፣ ብሩክ ሁን፤ የተባረከ ሀሳብ ነው ያመጣኸው። በሉ ሄደን እንፈልጋት። በዚያውም በሰላም ያሳደረን አምላክ በሰላም አውሎ፣ ቤዞና ቹቹንም በሰላም እንዲያገናኘልን እንፀልይ። ጉፈር ቀጃችንን ጠብቅ፤ ዙሮ መግቢያችን እሷ ነች» በማለት ተናግሬው ወደቤተክርስቲያን ሄዱ።

ማለዳ በመሆኑ ርግቦች በየጣራውና ግንቡ ላይ ክንፋቸውን እየዘረጉ ፀሀይ ሲሞቁ፣ ሌሎች በመንቆራቸው ጉያቸውን ይኮረኩራሉ። መሬት አርፈው ከሚለቃቀሙትም ሆነ ግንቡና ጣራው ላይ ካሉት ውስጥ ኩኩ መለኮቴን የሚመስል አንድም የለም። ደፋሩ ቢራቢሮ፣ ቹቹና አሞራው ፀሎታቸውን አድርሰው ከግቢው በመውጣት ላይ እያሉ ቹቹ፣

«ይሄኔ'ኮ ኩኩ መለኮቴ ከማይታይ ቦታ ትሆናለች» አለና የተለመደ የኩኩ መለኮቴን መጥሪያ ፉጨት አሰማ። ልክ የዚህን ጊዜ የቤዛዊት አባት፣ የቤዛዊት እናት፣ ቤዛዊት፣ ሶስና እና ሚጡ ወደቤተክርስቲያን ግቢ እየገቡ ነበር። ኩኩ መለኮቴም ከነበረችበት ቦታ በርራ ወደቹቹ ስትመጣ፣ ቹቹ «ኩኩ መለኮቴ!» በማለት ሮጠ።

የቹቹን ድምፅ ቤዛዊት ስትሰማና ቹቹን ስታየው አንድ ሆነ።

«ቹቹ! ቹ . . . ቹ!» በማለት ቤዛዊት ከሶስና እና ከሚጡ መሀል ወደቹቹ ተፈትልካ ሮጠች። ቹቹ ወደተጠራበት ፊቱን ሲያዞር ቤዛዊት፣ ከቤዛዊት ኋላ ሚጡ፣ ከሚጡ ኋላ ሶስና፣ ከሶስና ኋላ የቤዛዊት እናት፣ ከቤዛዊት እናት ኋላ የቤዛዊት አባት ወደእሱ ሲሮጡ ተመለከተና እሱንም ደስታ ፈንቅሎት «ቤዙ! ቤዙ! ቤ . . . ዙ» እያለ ወደሷ በረረ።



ቤዛዊት ቹቹን፣ ቹቹ ቤዛዊትን ይዘው በደስታ ይላቀሱ ጀመር:: ሲሮጡ የመጡት
ሚጡና ሶስናም ቹቹ ዘንድ ደረሱና አቅፈውት አለቀሱ::
በመጨረሻ ቹቹ ጓደኞቹን፣ አሞራውና ደፋሩ ቢራቢሮን ከቤዛዊት፣
ከሚጡ፣ ከቤዛዊት አባትና እናት ጋር አስተዋወቃቸው:: የቤዛዊት አባትና
እናትም ቹቹን ይቅርታ ጠየቁት:: ከዚያም የቤዛዊት አባት «ከዛሬ ጀምሮ ቹቹና
ጓደኞቹ ከኛ ጋር ይኖራሉ፤ የተቋረጠው የሽርሽር ፕሮግራማችንም ይቀጥላል::
የጉዳና ተዳዳሪ ህፃናትንም እንረዳለን:: ተመስገን!» በማለት እጆቹን ወደሰማይ
ሲዘረጋ ቤዛዊት፣ ቹቹ፣ ሚጡ፣ ሶስና፣ ደፋሩ ቢራቢሮ፣ አሞራውና የቤዛዊት
እናትም እጃቸውን ወደሰማይ ዘረጉ:: በመጨረሻም ጉፈሮን ጠርተው
ወደእነቤዛዊት ቤት ጉዞ ጀመሩ::